ከወያኔ የተጭበረበረ የምርጫ ሂደት በኋላ የሚቀጥለው ትግላችን ጥራትና ጥንካሬ የሚወስነው በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በውስጥም በውጭም ተንቀሳቅሰን በምንፈጥረውና ቀጣይነትንም ለማረጋገጥ ከዚህ እስከ ግንቦት ድረስ በምንወስዳቸው ተጨባጭ እርምጃዎች ነው:: የምንፈጥረው ህዝባዊ እምርታ ሰፋትና ጥልቀት ያለውና በተለይ በውጭ ደግሞ በድጋፍ ኮሚቴዎች አማካኝነት ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የሆነውን ያህል ሁኔታዎች ሳይሟሉ ዘው ብለው ወያኔ ምርጫ ውስጥ የሚገቡ ኃይሎች በሻማ ያዥነታቸው፣ በስነሥርዓት አድማቂነታቸው፣ በጊዜ ከህዝብ ጀርባ ተደራድሮ ወንበር አከፍላለሁ ብሉ ለተነሳው የወያኔ ሤራ ተባባሪነታቸው በግልጽ ስለሚታይ ህብረታችንን የመከፋፈልና ህዝባችንን ግራ የማጋባት አቅማቸው የዚያኑ ያህል ይሟሸሻል:: ይህ እምርታና ይህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ከሌለ ግን ተሳታፊዎቹ የሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የገባቸው፣ ህዝብ ውስጥ ገብተው ለመሳተፍ የሚደፍሩ አስተዋይ ኃይሎች፣ የማይሳተፉ ደግሞ የሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ያልገባቸው፣ የህዝብ ድምጽ የሚፈሩ አክራሪ ኃይሎች ተብለው በቀላሉ ይፈረጃሉ:: ለዲሞክራሲ መስፈንና ለነጻ ምርጫ የረጅም ጊዜ ትግል የተቋቋመው ህብረታችንም በዚህ በወያኔ ያልረባ ገርገር የተነሳ ይፍረከረክና ማን በዓላማው እንደጸናና ማን ከሀደት እንደፈጸመ ባልለየለት ሁኔታ ሁላችንም መሳለቂያ እንሆናለን::

ባጭሩ በዚህ ስብሰባ ላይ ዋና ዓላማ አድርገን መነሳት ያለብን በፓሪሱ ጥሪ ዙሪያ አዲስ ህዝባዊ እምርታ ለመፍጠር መሆን ይኖርበታል:: ለዚህም ተወያይተን በነጥብ በነጥብ ማስቀመጥ ያለብን የፖለቲካ ውሳኔ በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ እንዲሆን ሃሳብ ማቀረብ ይቻላል::

1ኛ/ በሃገራችን ዛሬ ከዛሬ አምስት ዓመት የተሻለ ለምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ የለም:: ከዚህ አንጻር ደግሞ ተቃዋሚ ኃይሎች ከዛሬ አምስት ዓመት ያልነበራቸውና ህዝቡንም በጋራ ሊቀሰቅሱበት የሚችሉበት፣ ዲሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ሊያደራጁበት የሚችሉበት ዲሞክራሲንና ነጻ ምርጫን የሚመለከት የጋራ ሰነድ አላቸው:: እስከ ህዳር መጨረሻ ድረስ ተመዝገቡ ብሉ ወያኔ ማዘዣ አውጥቷና በመጭው ሁለት ወራት / ከአንዳንዶች ጋር ብቻ በድብቅ ለመደራደር የሚያሴረውን በግልጽ ተቃውመን/ የፖሪሱን ጥሪ ደግፈን በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ በሰላማዊ ሰልፎችና በስብሰባዎች አማካኝነት መንቀሳቀስ:: በተለይ በውጭ ደግሞ ለቀጣዩም ትግል ሊያገለግል የሚችል የፈንድ ሬዚንግ ካምፔይን ማድረግ::

2ኛ/ እስከ ህዳር አጋማሽ ድረስ በዚህ ጥረታችን ያገኘነውን ፍሬ ለመገምገምና አንዳንድ ድርጅቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ የሚመዘገቡበትን ሁኔታ በጋራ ለመወሰን አንድ ስብሰባ መጥራት:: በዚህ ስብሰባ ላይ የተመዘገቡ ድርጅቶች ስለሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና የቅስቀሳና የፕሮፖጋንዳ ነጥቦች እንወያያለን፣ እንወስናለን:: እነዚህን ለማራመድ በተለይ ሃገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ስለሚያስፈልጋቸው የፋይናንስና የማቴርያል ድጋፍ እንወስናለን::

3ኛ/ ለምርጫ መመዝገብ ማለት የግድ ምርጫ ውስጥ መሳተፍ እንዳልሆነና አሁንም ቢሆን የተመዘገቡ ድርጅቶች ሁኔታዎች ካልተሟሉ እንደማይሳተፉ ግልጽ ማድረግና የተመዘገቡትም በዲሞክራሲ፣ በነጻ ምርጫ፣ በዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት፣ በህግ የበላይነትና በመሳሰሉት ጥያቄዎች በውስጥም በውጭም ያሉ የሃገራችን ዲሞክራቶች ያላቸውን አማራጭ ለህዝብ ለማድረስና ወያኔን ለመታገል ብቻ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጠው ትግሉ መድረክ ውስጥ መግባት

4ኛ/ በውጭ ያለው ተቃዋሚ ኃይል በነዚሁ ጥያቄዎች ዙሪያ ኢትዮጵያውያንን እያንቀሳቀሰ ለውስጡ ትግል ርዳታና ድጋፍ ማስገኘትና ከዚህ አልፎ የዲሞክራቶችን አማራጭ እያጎላና የወያኔን የሸፍጥ ሂደት እያጋለጠ በዲፕሎማሲው መስክ የተቀነባበረ ዘመቻ ማድረግ::ትግሉንም ቀጣይነት ያለው ለማድረግ ድጋፍ ኮሚቴዎችን በያለበት ማደራጀት::

5/ ይህ የተቃዋሚዎች ሂደት ከዳር እስከዳር በውይይትና በጋራ ውሳኔ የሚከናወን
ሂደት መሆን ያለበት ስለሆነ በዚህ በአራት አምስት ወር የተገኘውን ፍሬ ለመገምገምና የ
መሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ጥያቄ ላይ ለመወያየት ብንሳተፍ እንዴት? ባንሳተፍ ቀጣዩ ስት
ራቴጂ ምንድን ነው? በሚሉት ጉዳዮች ላይ የጋራ ውሳኔ ለመድረስ ከምርጫው አንድ ወር ሲ
ቀር እንደገና ሌላ ስብሰባ መጥራት::

6. የመሳተፍ ያለመሳተፉ ጥያቄ እስከመጨረሻው ባይወሰድና ዊዝድሮዋል ከመጣ አልጀ
ርያ እንደተደረገው በምርጫው እለት ዋዜማ ውሳኔ ቢደረግበት የሚሉ ሃሳቦች አሉ:: ከዚህ
ይልቅ የሚመረጠው ውሳኔው ቢያንስ አንድ ወር ቢቀድም ነው:: አንደኛ/ ይህ ከሆነ ወያኔ
እንደለመደው ብቻውን ሲሮጥ፣ ስነሥርዓት አድማቂዎች ካገኘ እነሱም ሥነሥርዓት ሲያደምቁ
ለማጋለጥ እንዲቻል አንድ ወር ያህል ቢሰጥ ጥሩ ነው:: ሁለተኛ/ ተሳትፍ ከሌለ ህዝቡንም
ያው የተጠየቀው እንደኛውም አልተሟላምና ይህንን ፌዝ በይኮት አርግ ለሚለው ቅስቀሳ ጊዜ
ለመስጠት:: ሶስተኛ/ አሁን ባለው ሁኔታ ወያኔዎች የውጭ ታዛቢ አንፈልግም ይበሉ እንጂ
እነሱ የሚመርጧቸው ታዛቢዎች /አሰድ፣ ኢጋድ፣ አንዳንድ መንግሥታትና ዲፕሎማቶች / ይና
ራሉ:: ታዛቢ አይጋበዝም የተባለው ነጻ አስተሳሰብ ያላቸውን ኤንጂኦዎች ለማገድ ነው::ይ
ህም በመሆኑ መንግሥት የመረጣቸው ታዛቢዎች እንዳይገኙ ቅስቀሳ ለማድረግ አንድ ወር ያህል
ያስፈልጋል::